# የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ)

## የ2007 ዓ.ም

### የምርጫ መወዳደሪያ ማኒፊስቶ

የኢዴፓ የ2007 ዓ.ም

የምርጫ መወዳደሪያ ምልክት

"አበባ"

**የትኩረትነ ጥቦች:**

1ኛ- ትኩረት፤ - የኑሮ ውድነትን ማቃለል

2ኛ- ትኩረት፤ - ለዜጎች ሰፊ የስራ እድል መፍጠር

3ኛ- ትኩረት፤ - ረሃብን ማስወገድና ደህነትን መቀነስ

4ኛ- ትኩረት፤ - መልካም አስተዳደርን ማስፈን

**ኢዴፓ ከሁሉም የህብረተሰብ ክፍል የበለጠ ለወጣቱ ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡**

## ኢዴፓ የዛሬወና የወደፊቱ ትውልድ ፓርቲ!

ኢዴፓ

2007 ዓ.ም

ማውጫ

# የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) የ 2007 የምርጫ መወዳደሪያ ማኒፌስቶ


መግቢያ ........ 2

1.ዓላማ ........ 3

2. የዓላማ ማስፈጸሚያ ስልቶች ........ 3

3. ኢዴፓ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው የኀብረተሰብ ክፍል ........ 4

4. የኢዴፓ የ 3 ኛ አማራጭነት የሚገለጽባቸው የትግል ስልቶች ........ 4

5. ኢዴፓ ለመንግስት ስልጣን ቢበቃ በቅደም ተከተል ቀዳሚ ትኩረት ሰጥቶ የሚተገብራቸው አጀንዳዎች........ 6

5.1- ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች ........ 7

5.1.1 የኑሮ ውድነትን ለማቃለል የሚወሰዱ እርምጃዎች ........ 7

5.1.2- ከዚህ በላይ በተዘረዘሩትና የኑሮ ውድነትን ለማቃለል ተብለው በሚወሰዱ እርምጃዎች ምክንያት የሚፈጠረውን የመንግስት ገቢ መቀነስ ለማካካስ የሚወሰዱ እርምጃዎች........ 8

5.1.3- ሰፊ የስራ እድልን ለዜጎች ለመፍጠር የሚወሰዱ እርምጃዎች........ 9

5.1.4- ረሃብን ለማስወገድና ድህነትን ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃዎች........ 10

5.1.5- በኢኮኖሚ ረገድ ትኩረት የሚሰጣቸው ሌሎች ልዩ ልዩ ጉዳዮች........ 12

5.2- በማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚወሰዱ እርምጃዎች........ 13

5.2.1- የትምህርት አገልግሎትን በጥራት ለማዳረስ የሚወሰዱ እርምጃዎች........ 13

5.2.2- የጤና አገልግሎት በስፋትና በጥራት ለማዳረስ የሚወሰዱ እርምጃዎች........ 15

5.2.3- በመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዶችን ሙስናንና ብክነትን ለማስወገድ፣በአጠቃላይም የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የሚወሰዱ እርምጃዎች........ 15

5.2.4- የመኖሪያ ቤት ችግርን ለመፍታት የሚወሰዱ እርምጃዎች........ 16

5.2.5- የተፈጥሮ ሀብትንና የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ የሚወሰዱ እርምጃዎች........ 17

5.2.6- ልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች........ 17

5.3- በፖለቲካ ጉዳዮች ዙሪያ የሚወሰዱ እርምጃዎች ........ 17

5.3.1- ለአገሪቱ አንድነት መጠናከርና ለተሻለ የኢኮኖሚ እድገት የሚያበቁ ህገ-መንግስታዊ ማሻሻያዎች ማድረግ........ 18

5.4- የውጭ ጉዳይን በተመለከተ ኢዴፓ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች........ 19


## የኢትዮጵያውያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ)

## የ 2007 ዓ.ም የብሄራዊ ምርጫ መወዳደሪያ ማኒፌስቶ

# 2007 ዓ.ም

## መግቢያ

አገራችን ኢትዮጵያ ከብዙዎቹ የዓለማችንና የአፍሪካ አገሮች በተለየ የረዥም ጊዜ ታሪክ ያላት አገር መሆኗንና የሰው ልጆች መገኛ መሆኗ በከርሰ ምድሯ ውስጥ የተገኙ ሚሊዮን አመታትን ያስቆጠሩት ቅሪተ አካላት ህያው ምስክር ናቸው:: ምንም እንኳን የረጅም ጊዜ ታሪክ ያላት አገር ብትሆንም የታሪኳ አብዛኛው ክፍል የእርስ በርስ ጦርነትና ግጭት ሆኖ አልፏል :: የኢትዮጵያ የአገር ምስረታ ሂደት በአንድ በኩል በኃይልና መስፋፋት እንቅስቃሴ፤ በሌላ በኩል ደግሞ በተለያዩ የአንድነትና አብሮ የመኖር መስተጋብሮች ብዙ ፈተናዎችን አልፎ ከዛሬ የደረሰ ቢሆንም አገሪቱ በሁለንተናዊ መልኩ ከእድሜዋ በሚመጥን የዕድገት ደረጃ ላይ መድረስ አልቻለችም:: የ 21 ኛው ክፍለ ዘመኗ ኢትዮጵያ ከብዙ ከኋላዋ ከተፈጠሩ አገሮች በተለየና በባሰ የፖለቲካ መቻቻልና መረጋጋት የሌለባት፣ በከፋ ድህነት ውስጥ የምትገኝና የተለያዩ ማህበራዊ ቀውሶች የተንሰራፉባት አገር ሆናለች::

በአገራችን ዘመናዊ የፖለቲካ እንቅስቃሴ ከተጀመረ ከ 50 ዓመታት በላይ ያስቆጠረ ቢሆንም ከንጉሡ የአገዛዝ ዘመን መወገድ በኋላ የተተኩት አገዛዞች የፖለቲካ አስተሳሰባቸው በጥላቻና በመጠፋፋት ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በአገራችን የተረጋጋና ዘላቂነት ያለው የፖለቲካ ሥርዓት እስከ አሁን ሊፈጠር አልቻለም:: በአንድ በኩል የግራ ፖለቲካ በሂደትና በመቻቻል ሳይሆን በስር ነቀል አብዮታዊ ለውጥና በአንድ ፓርቲ ፍጹማዊ የበላይነት የሚያምን በመሆኑ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ከ 196 ዐዎቹ ጀምሮ እስከ ዛሬ ድረስ የአገሪቱን ፓለቲካ በገዥነትም ሆነ በተቃዋሚነት በበላይነት የተቆጣጠሩት ኃይሎች በግራ ፖለቲካ አስተሳሰብ ተኮትኩተው ያደጉ የአንድ ትውልድ አባላት በመሆናቸው ምክንያት ፖለቲካችን ወደ አዲስና ጤናማ ምዕራፍ መሸጋገር ተስኖት እየተንገዳገደ ይገኛል:: በ 196 ዐዎቹ የግራ ፖለቲካ አራማጆች ዘመኑንና የበላይነት ዕድሉን የተቀማው አዲሱ ትውልድ በወቅቱ የፖለቲካ ሂደት የጐላ ሚና ሊኖረው ባለመቻሉም የወቅቱ የአገራችን ፖለቲካም ሆነ ፖለቲከኞች ባለፈው ታሪክ ተቀይደው ለዛሬዋና ለነገዋ ኢትዮጵያ የሚመጥን አዲስና ቀጣይነቱ አስተማማኝ የሆነ ራዕይ ይዘው መምጣት አልቻሉም::

ከዚህ መሠረታዊ የፖለቲካ ችግር በመነጩ የአገራችን ፖለቲካ "ገዥ ፓርቲ" እና "ተቃዋሚ" በሚሉ ሁለት ጐራዎች፤ ነገር ግን እርስ በርሱ ተመጋጋቢና ተደጋጋፊ የሆነ አንድ አይነት የጽንፈኝነት ባህል ባላቸው የፖለቲካ ኃይሎች ቁጥጥር ስር በመውደቁ የኢትዮጰያ ሕዝብ የተሻለና አዲስ አማራጭ የሚያገኝበት ዕድል ተነፍጐት ኖሯል:: ይህንን የአገራችንን ፓለቲካ ወደ ፊት እንዳይራመድ ያደረገውን መሰረታዊ ችግር የተገነዘበው ኢዴፓ ባለፉት አስር አመታት እራሱን ገዥው ፓርቲም ሆነ ሌሎች ታቃዋሚ ፓርቲዎች ከሚያራምድት የፅፈኝነት አ k ም በማራቅ አገራዊ መግባባትንና መቻቻልን የሚያጠናክር በምክንያታዊነትና በሀቀኝነት ላይ የተመሰረተ የሦስተኛ አማራጭነት የፓለቲካ ስልት ሲያራምድ ቆይቷል:: ይህንን መሠረታዊ የፖለቲካ ክፍተት የተገነዘበው የኢትዮጵያዊያን ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ (ኢዴፓ) ዘንድሮም በሚካሄደው አገር አቀፍ ምርጫ "ኢዴፓ የዛሬውና የነገው ትውልድ ፓርቲ!" በሚል መፈክር እራሱን 3 ኛ አማራጭ አድርጐ ለምርጫ ቀርቧል:: የኢዴፓ የ 3 ኛ አማራጭነት ሚና ከሁሉም በላይ በፓርቲው የትግል ስልትና አቀራረብ አዲስነት የሚገለፅ ሲሆን በሚያራምዳቸው የተለያዩ አገራዊ አጀንዳዎችም ዙሪያ ይንፀባረቃል:: በዚህ የኢዴፓ የ 3 ኛ አማራጭነት ሚና ሕዝቡ በተለይም አዲሱ ትውልድ እስካሁን ከነበረው "ገዥ ፓርቲ" እና "ተቃዋሚ" ከሚል ሁለት የጠበበ አማራጭ ወጥቶ ለዛሬዋና ለነገዋ ኢትዮጵያ የሚበጀውን ፓርቲ የፖለቲካ "ጐራን" ሳይሆን

## 2007 ዓ.ም

የፖለቲካ አማራጭ ኃሳብን መሠረት አድርጐ እንዲመርጥ እድል ይፈጥርለታል፡፡ ከዚህ እምነት በመነሳት ኢዴፓ የትውልዱ ምርጫ መሆን ይገባኛል ብሎ የሚያምንባቸውን አማራጭ ስልቶቹንና በተለያዩ አገራዊ አጀንዳዎች ዙሪያ የሚያራምዳቸውን አቋሞች በዚህ የምርጫ ማንፌስቶ ይዞ ቀርቧል፡፡

በ 2007 ዓ.ም ላይ በኢትዮጵያ የሚካሄደው ምርጫ ነፃ ፍትሃዊና አሳታፊ እንዲሆን ኢዴፓ የበኩሉን ጥረት እንደከዚህ ቀደሙ በቁርጠኝነት እያደረገ ይገኛል፡፡ የዘንድሮ ምርጫ ከዚህ በፊት ከተደረጉት ምርጫዎች በቂ ትምህርት የተገኘበትና ከነበሩት ችግሮች በመነሳት ነፃ ፍትሃዊና ዲሞክራሲያዊ ምርጫ እንዲሆን ኢዴፓ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት አጠንክሮ የሚሰራ ሲሆን መንግስትም ሁሉንም ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሊያሳትፍ የሚችልና ከወገንተኝነትና ከአድሎ የፀዳ የመወዳደሪያ ሜዳ ማመቻቸት ይኖርበታል፡

ለ 2007 ዓ.ም ምርጫ ህዝብ ራሱ የመንግስት ሥልጣን ምንጭ መሆኑን በተግባር የሚያረጋ
ጥበት፣ ለፖለቲካ ሥልጣን የሚወዳደሩ የፖለቲካ ፓርቲዎችና ግለሰቦች እኩል የመወዳደሪያ ሜዳ የሚያገኙበት፣ ዓለም አቀፍ ተቀባይነት ያላቸው የምርጫ መርሆዎች ሥራ ላይ የሚውሉበት እንዲሆን ከፍተኛ ፍላጎትና ትግል የማካሄድ ቁርጠኝነት አለው ፡፡ ይህንን ምርጫ እንደአለፉት ምርጫዎች ሁሉ መንግስትና ገዥው ፓርቲ የራሱን ፀረ-ዴሞክራሲያዊ ባህሪ ለመሸፈንና በህዝብና በዲፕሎማቲክ ማህበረሰቡ ዘንድ ድጋፍ ያለው አስመስሎ ለመታየትና በየአምስት አመቱ የሚመጣ የመርሃ ግብር ማሟያ አድርጐት ለማለፍ የሚሞክር ከሆነ ትልቅ ታሪካዊ ስህተት ነው፡፡ የተፎካካሪ ፓርቲዎች ወደ ስልጣን መምጫ መንገድ በህዝብ ፈቃድና ፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንዲሆን የምርጫ ሜዳውና ምህዳሩ ለሁሉም ተፎካካሪ ፓርቲዎች የተመቻቸ እንዲሆን መንግስት ቁርጠኝነት ማሳየት አለበት፡፡

ኢዴፓ በነፃ ምርጫ፣ በህዝብ ፈቃድና ሰላማዊ በሆነ የስልጣን ሽግግር የመንግስት ስልጣን የሚያዝበትንና የሚለቀቅበትን አዲስ ምዕራፍ በኢትዮጵያ እንዲጀመር ትግል ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ አሁንም ሆነ ወደፊት ይህንኑ ምክንያታዊና የመቻቻል ፖለቲካ ይዞ በመቀጠል በሰላማዊ ትግል መንግስት ለመቀየር እንዲቻል በማንፌስቶው የቀረቡትን ሀገራዊ አጀንዳዎች መራጩ ህዝብ መዝኖ ኢዴፓን በመደገፍ ድምጹንና ውክልናውን እንዲሰጥ ጥሪያችን እናቀርባለን፡፡

## 1.ዓላማ

የኢዴፓ የፖለቲካ ዓላማ የእያንዳንዱ ዜጋ የግልና የጋራ መብት የተከበረባትና የሊበራል ዴሞክራሲ አስተሳሰብ የነገሠባት ኢትዮጵያን መገንባት ሲሆን፤ የኢኮኖሚ ዓላማው ደግሞ የነፃ-ገበያ ሥርዓት የሰፈነባትና ሁሉም የአገሪቱ ዜጋ በየደረጃው ተጠቃሚ የሆነባት የበለጸገች ኢትዮጵያን መገንባት ነው፡፡ ኢዴፓ ከእነዚህ መሠረታዊ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ዓላማዎች በመነጨም ኢትዮጵያ በሁለንተናዊ መልኩ መልካም አስተዳደርና ማህበራዊ ፍትህ የነገሠባት አገር እንድትሆን ይታገላል፡፡

## 2. የዓላማ ማስፈጸሚያ ስልቶች

ኢዴፓ በኢትዮጵያ የፖለቲካ፣ የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ዓላማዎቹ በሰከነና ዘላቂነት ባለው መልኩ እንዲፈጸሙ የሚያስችል ስልት ያራምዳል፡፡ ስልቱ ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር በሚጣጣም ሁኔታ የተለዋዋጭነትና የተፈጻሚነት /Pragmatic/ ባህሪ

ያለው እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የፓርቲውን የአፈጻጸም ስልት የፓርቲውን የአጭር ጊዜ መነሻና የእሩቅ ጊዜ መድረሻ ግብ ለያይቶ የሚያይ ሲሆን አገሪቱ በአሁኑ ወቅት በፖለቲካና በኢኮኖሚ ረገድ የምትገኝበትን ሽግግር በአግባቡ ግምት ውስጥ ያስገባ ይሆናል፡፡

## 3. ኢዴፓ ቅድሚያ ትኩረት የሚሰጠው የኅብረተሰብ ክፍል

ኢዴፓ የሊበራል ዴሞክራሲ መስመርን የሚከተል ፓርቲ እንደመሆኑ መጠን ለእያንዳንዱ ዜጋ መብትና ጥቅም መከበር የሚታገል ፓርቲ ነው፡፡ ሆኖም የዛሬዋም ሆነች የነገዋ ኢትዮጵያ አጠቃላይ ዕጣ ፈንታ ሊወሰን የሚችለውና የሚገባው በወጣቱ ትውልድ ስለሆነ ኢዴፓ በቅደም ተከተል በሚተገብራቸው ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ለወጣቱ የኅብረተሰብ ክፍል ልዩና ቅድሚያ ትኩረት ይሰጣል፡፡ ኢዴፓ በአሁኑ ወቅት አገሪቱ ወደተሻለ ፖለቲካዊም ሆነ ኢኮኖሚያዊ ደረጃ መሸጋገር ያልቻለችው የ1960ዎቹና ከግራ ፖለቲካ አስተሳሰብ ጋር አብሮ ያደገው ትውልድ ለረዥም ጊዜ የአገሪቱን ዕጣ-ፈንታ በመወሰን ረገድ የወሳኝነቱን ድርሻ ይዞ በመቀጠሉ ነው የሚል ጽኑ እምነት ስላለው ይህ ሁኔታ ተለውጦ አዲሱ ወጣት ትውልድ (ወንድ/ሴት) በሁሉም መስክ የበላይነቱንና የወሳኝነቱን ድርሻ በአገሪቱ እንዲይዝ የሚያስችል አቅጣጫ ይከተላል፡፡ ያለፈውን ትውልድ በጎ ልምዶችና ተሞክሮዎች በአግባቡ የመጠቀሙ አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ በአንድ በኩል ህጻናትና ታዳጊ ወጣቶች በሁለንተናዊ መልኩ ብቁና አገር ወዳድ ዜጋ ሆነው የሚያድጉበትን ሁኔታ በማመቻቸት፤ በሌላ በኩል ደግሞ በአሁኑ ወቅት ከ20-45 ዓመት የዕድሜ ክልል ውስጥ የሚገኘው ለሥራ ብቁ የሆነው ትውልድ ሙሉ በሙሉ ወደ ስራ ዓለም ገብቶ የአገሪቱ ዋና አንቀሳቃሽ ኃይል እንዲሆን የሚያስችሉ ተግባራትን በስፋትና በቀዳሚነት ያከናውናል፡፡ በተለይም እስከ 30 ዓመት የሚገኘውና ረጅም የስራ ዕድሜ ያለው ወጣት ትውልድ በኢዴፓ ልዩና ከፍተኛ ትኩረት የሚያገኝ የኅብረተሰብ ክፍል ይሆናል፡፡ ይህንን ዓላማ በብቃት ለመተግበር ይቻል ዘንድም ኢዴፓ ከፓርቲው አባልነት እስከ አመራር ድረስ ከ90 በመቶ ባላነሰ መጠን በወጣቱ ትውልድ የተገነባ ፓርቲ የመሆኑን እውነታ የበለጠ አጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል፡፡

## 4. የኢዴፓ የ3ኛ አማራጭነት ሚና የሚገለፅባቸው የትግል ስልቶች

**4.1-** ኢዴፓ - በእስካሁኑ የአገራችን የፖለቲካ ባህል ከተለመደው በጭፍን የመደገፍና በጭፍን የመቃወም ጤናማ ያልሆነ ስልት ነፃ በሆነ መንገድ ፖለቲካን በምክንያታዊነት ያራምዳል፡፡ ባደጉትና በሰለጠኑት አገሮች እንደሚታየው በእኛም አገር አንድ የፓለቲካ ኃይል ከሌላው የተሻለ ለአገርና ለህዝብ ጥቅም የቆመ መሆኑን ለማሳየት መሞከር የሚገባው ሌሎችን በጥላቻ በማየትና በጠላትነት በመፈረጅ ሳይሆን የራሱን አማራጭ ሃሳቦች ለሕዝብ አቅርቦ በማሳመን መሆን ይገባዋል ብሎ ኢዴፓ ያምናል፡፡ አንድ ሐሳብ ከማንም ይምጣ ከማን ለአገርና ለሕዝብ እስከጠቀመ ድረስ በኢዴፓ ይደገፋል፡፡ ሐሳቡ ለአገርና ለሕዝብ የማይጠቅም ሆኖ ከተገኘ ደግሞ በኢዴፓ ይነቀፋል፡፡ በሁሉም አገራዊ ጉዳዩች ላይ በምክንያት የተደገፉ የራሱን አማራጭ ሐሳቦች በዝርዝር እያቀረበ ጨዋና ስልጡን ትግል ያካሂዳል፡፡

**4.2-** ኢዴፓ- የአገራችን ፖለቲካ ከእንግዲህ ከጥላቻ፣ከኩርፊያና ከስሜታዊነት ባህል ተላቆ በምትኩ የመደማመጥ፣ የመቻቻል፣ የመደራደር፣ እውቅና የመስጠትና በጋራ ጉዳዮች ዙሪያ አብሮ የመስራት የፖለቲካ ባህል እንዲጐለብት ይታገላል፡፡ ለዚህ ዓይነቱ የፖለቲካ ባህል መጀመርና መጠናከርም አርዓያና ምሳሌ ሆኖ ይቀርባል፡፡

**4.3-** ኢዴፓ- እንደአመችነቱ ቦታና ጊዜ እየመረጠ ሳይሆን የመደራጀት መብት ከሀገሪቱ ህገ-መንግሥት እስካልተፋቀ ድረስ በማንኛውም ወቅትና ሁኔታ ሰላማዊ ትግልን ብቸኛ የትግል ስልት አድርጐ ያራምዳል፡፡ኢዴፓ ሰላማዊ ትግልን ብቸኛ ስልት አድርጐ ከማራመዱም በተጨማሪ ከሰላማዊ ትግል ውጭ የሚካሄድን ማናቸውም ዓይነት የአመፅና የጦርነት አማራጭን በግልፅ ያወግዛል፡፡

**4.4-** ኢዴፓ- ለሕግ የበላይነት፣ ለተቋማት ግንባታና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ሂደት ልዩ ትኩረት የሚሰጥ የትግል እንቅስቃሴ ያደርጋል፡፡ በአንድ በኩል ለአገሪቱ ሕጐችና ተቋማት ተገቢውን አክብሮትና ዕውቅና እየሰጠ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ምክንያታዊ ትችትና ተቃውሞ እያቀረበ ድክመት የሚታይባቸው ሕጐችና ተቋማት ተገቢ ማሻሻያና ለውጥ እየተደረገባቸው ዴሞክራሲያዊ ሂደቱ ቀጣይነት ያለውና የበለጠ ጠንካራ እንዲሆን የሚያስችል ትግል ያደርጋል፡፡

**4.5-** ኢዴፓ - በአገሪቱ ለሚታዩ ሁለንተናዊ ችግሮች ሁልጊዜ በሥልጣን ላይ የተቀመጡ መንግሥታትንና ሌሎች የፖለቲካ ኃይሎችን ብቸኛ ተጠያቂ አድርጐ የመመልከት መርህን አይከተልም፡፡ ኢዴፓ ድርሻችን የተለያየ ቢሆንም ሁላችንም የአገሪቱ ችግሮች አካል ነን፤ ሁላችንም የወደፊቱ የአገሪቱ ችግሮች የመፍትሔ አካልም እንሆናለን ብሎ ያምናል፡፡ ኢዴፓ የኢትዮጵያ የፓለቲካ ኃይሎች በመካከላችን ልዩነቶች ያሉ መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በጋራ አገራዊ ጉዳዩቻችን ዙሪያ በጋራ መስራት እስካልቻልን ድረስ የምንመኛትን ኢትዮጵያ መገንባት አዳጋች መሆኑን ይገነዘባል ፡፡

**4.6-**ኢዴፓ- ወቅታዊ በሆኑ ተለዋዋጭ ፓለቲካዊ ስሜቶች በሚፈጠሩ የሕዝብ አስተያየቶች (public opinion) እና ዘላቂ በሆነ የሕዝብ ፍላጐትና ጥቅም መካከል ያለውን መሠረታዊ ልዩነት በውል የሚገነዘብ ፓርቲ ነው፡፡ ስለሆነም በሕዝብ ዘንድ ጊዜያዊ ድጋፍና ተወዳጅነት ለማግኘት ሲል ያለበቂ ጥናትና መረጃ በስሜት በመነሳት "ሕዝብ ምን ለማዳመጥ ይፈልጋል?" የሚል የእወደድ ባይነት (populist) ፖለቲካ ከማራመድ እራሱን ያርቃል፡፡ ከሕዝብ የሚነሱ ጥያቄዎችን በቂ ጊዜ ወስዶና ጥናት አድርጐ ከተጨባጭ ሁኔታው ጋር የሚጣጣም መፍትሄ ለሀገሪቱ ችግሮች ያቀርባል፡፡ አገርንና ሕዝብን በዘላቂነት የሚጠቅም ሆኖ እስካገኘው ድረስ ጊዜያዊ የሕዝብ ትችትና ተቃውሞን በፀጋ በመቀበል ጭምር የኃቀኝነት ፖለቲካን በጽናትና በድፍረት ያራምዳል፡፡ ከልቡ ባላመነበት ጉዳይ አስመሳይ አቋም በማራመድ ጊዜአዊ ተወዳጅነትን ለማግኘት ከመሞከር ይልቅ ለአገርና ለሕዝብ ይጠቅማል ብሎ ያመነበትን አስተሳሰብ በድፍረት በማራመድ ከመሸበት የማደርን አቋም ያራምዳል፡፡

**4.7-**ኢዴፓ - በእስካሁኑ የአገራችን የፖለቲካ ባህል እንደተለመደው ተቀናቃኝ ኃይልን ተገቢ ባልሆነ ፍረጃ፣ በሴረኝነት በስም ማጥፋትና በአሉባልታ ዘመቻ የማጥቃት ስልትን አያራምድም፡፡ ይህንን ዓይነት ተገቢ ያልሆነ ስልት በመጠቀም ሊያጠቁት

የሚሞክሩ የፖለቲካ ኃይሎችን ግን በመረጃ የተደገፈ ግልጽ ክርክርና ትችት በማቅረብ፣ በአጀንዳ ጥራትና በሐሳብ የበላይነት ለማሸነፍ የሚያበቃውን ትግል በጽናት ያካሂዳል፡፡

**4.8-** ኢዴፓ- ከዚህ በላይ የተዘረዘሩ የ3ኛ አማራጭነት ሚና መገለጫዎች የሆኑ የትግል ስልቶች የመጨረሻ ግብ ሰላማዊ የሥልጣን ሽግግርን በአገሪቱ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በጽኑ መሠረት ላይ እንዲተከል ማድረግ ነው ብሎ ያምናል፡፡ የኢዴፓ የሰላማዊ ትግል የመጨረሻ ግብ በአገራችን ፖለቲካ የመንግሥት ሥልጣን በጠመንጃና በኃይል የሚያዝበት አዙሪት ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተበጥሶ ሕዝቡ በሰላማዊ፣ ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ብቻ የራሱን አስተዳደር የሚመርጥበትና የሚሽርበት ዘላቂነት ያለው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን በኢትዮጵያ እንዲሰፍን ማደረግ ነው፡፡

በአጠቃላይ ኢዴፓን ከሚያራምዳቸው ፓለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ አጀንዳዎቹ በላይ ከገዡው ፓርቲም ሆነ ከአብዛኛዎቹ ተቃዋሚ ፓርቲዎች የተለየና የተሻለ የሚያደረጉትን እነዚህ የ3ኛ አማራጭነት ስልቶቹ ናቸው፡፡ ኢዴፓ እነዚህን ስልቶች በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ከመቀበል በላይ በተግባር እየፈፀማቸው የሚገኝ በመሆኑ በአንድ አገር አዲስ የፓለቲካ ባህል ቀድሞ ጀማሪና ተዋናይ በመሆን ሊከፈል የሚገባውን መስዋዕትነት እየከፈለ ይገኛል፡፡ ከአገራችን አሮጌ የፖለቲካ ባህልና ከግራ ፖለቲካ አስተሳሰብ ጋር ተጣብቶ ያደገው የአገራችን የፖለቲካ ኃይል በቀላሉ ከጥላቻና ከመጠፋፋት የፖለቲካ ባህ

ሊላቀቅ አይችልምና ይህ ነባራዊ ሁኔታ የኢዴፓን ትግል ከባድና መራራ እንደሚያደርገው አስቀድሞ የሚገመት ነው፡፡ ይሁን እንጂ የዛሬውና የመጭው ትውልድ ፖለቲካ ከዚህ አይነቱ የምክንያታዊነት ፖለቲካ ውጭ ሊሆን አይገባም ብሎ ስለሚያምን ኢዴፓ ራሱን የዛሬውና የወደፊቱ ትውልድ ተመራጭ ፓርቲ አድርጎ አቅርቧል፡፡ የሚያራምደው የምክንያታዊነት ፖለቲካ የትውልዱ ባህሪ መገለጫ ሆኖ በአገሪቱ ፖለቲካ የበላይነቱን እስከሚይዝ ድረስም የጀመረውን ትግል አጠናክሮ ይቀጥላል፡፡

# 5. ኢዴፓ ለመንግሥት ሥልጣን ቢበቃ በቅደም ተከተል ቀዳሚ ትኩረት ሰጥቶ የሚተገብራቸው አጀንዳዎች

ኢዴፓ ግንቦት 16 ቀን 2007 ዓ.ም በአገራችን በሚካሄደው አገራዊ ምርጫ የሕዝብን ይሁንታ አግኝቶ ከተመረጠ በአገሪቱ ዘላቂ የፖለቲካ መረጋጋት ለመፍጠር፣ ቀጣይነት ያለውና በየደረጃው የሚገኘውን የኅብረተሰብ ክፍል ተጠቃሚ የሚያደርግ የኢኮኖሚ ዕድገት ለማምጣትና ማህበራዊ ደህንነትን በአገሪቱ ለማስፈን የሚያስችሉት የተለያዩ አማራጭ አጀንዳዎችን ይዞ ቀርቧል፡፡ ኢዴፓ በዘንድሮው ምርጫ የሚያቀርባቸው አጀንዳዎች ሁሉንም አገራዊ ችግሮች የሚዳስሱ ቢሆንም በቅደም ተከተል አኳያ፡-

1ኛ. ትኩረት፤ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች

2ኛ. ትኩረት፤ ማህበራዊ ጉዳዮች

3ኛ. ትኩረት፤ ፓለቲካዊ ጉዳዮች በቅደም ተከተል የሚይዙ ይሆናል፡፡

የመጀመሪያ ቀዳሚ ትኩረት ከተሰጣቸው ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች መካከልም የሚከተሉት ሦስት ጉዳዮች በቅደም ተከተል ቀዳሚውን ትኩረት ያገኛሉ ፡፡ እነሱም፤-

**2007 ዓ.ም**

1ኛ- ትኩረት፤የኑሮ ውድነትንና የዋጋ ግሽበትን ማቃለል፤

2ኛ- ትኩረት፤ለዜጎች ሰፊ የስራ ዕድል መፍጠር፤

3ኛ- ትኩረት፤ረሃብን ማስወገድና ድህነትን መቀነስ ናቸው፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ትኩረት ከተሰጣቸው ማህበራዊ ጉዳዮች መካከልም የሚከተሉት አምስት ጉዳዮች በቅደም ተከተል ቀዳሚውን ትኩረት ያገኛሉ፡፡ እነሱም፤-

1ኛ- ትኩረት፤የትምህርት አገልግሎትን በጥራት ማዳረስ፤

2ኛ- ትኩረት፤የጤና አገልግሎትን በስፋትና በጥራት ማዳረስ፤

3ኛ- ትኩረት፤በመንግስት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዶችን፤ ሙስናንና ብክነትን ማስወገድ፤

4ኛ- ትኩረት፤የመኖሪያ ቤት ችግርን መፍታት፤

5ኛ- ትኩረት፤ለአካባቢ ደህንነትና ለተፈጥሮ ሃብት ጥበቃ ሰፊ ትኩረት መስጠት ናቸው፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ትኩረት ከተሰጣቸው የፖለቲካ ጉዳዮች መካከል የሚከተሉት አራት ጉዳዮች በቅደም ተከተል ቀዳሚውን ትኩረት ያገኛሉ፡፡ እነሱም፤-

1ኛ. ትኩረት፤ሰላምና መረጋጋትን ማስፈን፤

2ኛ. ትኩረት፤ብሔራዊ መግባባትን በመፍጠር የአገሪቱን አንድነት ማጠናከር፤

3ኛ. ትኩረት፤የህግ የበላይነትን በማረጋገጥ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ማስከበር፤

4ኛ. ትኩረት፤ለአገሪቱ አንድነት መጠናከርና ለተሻለ የኢኮኖሚ እድገት የሚበጁ ሕገ-መንግሥታዊ ማሻሻያዎችን ማድረግ ናቸው፡፡

ከነዚህ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ውስጥ የመጀመሪያውን ትኩረት የሚያገኘው የሰላምና መረጋጋት ጉዳይ ለፖለቲካ ብቻ ሳይሆን ለኢኮኖሚና ማህበራዊ አጀንዳዎች ተፈጻሚነት ጭምር ወሳኝና የመጀመሪያ ቅድመ-ሁኔታ በመሆኑ በማንኛውም ጊዜና ቦታ በፓርቲው ቋሚ ትኩረት አግኝቶ የሚተገበር አጀንዳ ይሆናል፡፡

## 5.1- የኢኮኖሚ ጉዳዮች

## 5.2- የኑሮ ውድነትንና የዋጋ ግሽበትን ለማቃለል የሚወሰዱ እርምጃዎች

የኢዴፓ የመጀመሪያ ቀዳሚ እርምጃ በአሁኑ ወቅት በአገራችን የተንሰራፋውንና የሕዝቡን የእለት ተዕለት ኑሮ እጅግ መራራ ያደረገውን የኑሮ ውድነት ማቃለል ይሆናል፡፡ የኑሮ ውድነቱን ለማቃለል የሚከተሉትን እርምጃዎች ይወስዳል፡፡

ሀ- ባለፉት 10 ዓመታት እንደገና ወደኋላ ሊመለስ በማይችል መጠን ካደገው የኑሮ ውድነት ጋር የተመጣጠነ በጥናት ላይ የተመሰረተ የደመወዝ ጭማሪ ለመንግሥት ሰራተኞችና ለጡረተኞች ይደረጋል፡፡ የመንግስት ሰራተኞችን መነሻ ደመወዝ

/Minimum wage/ 1000.00 ብር እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የሁሉም ጡረተኞች መነሻ ደመወዝ 700.00 ብር እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ለ- በግል ድርጅቶች ተቀጥረው ለሚሰሩ ዜጐች ከወቅቱ የኑሮ ውድነት ጋር የሚመጣጠን በጥናት ላይ የተመሰረተ አዲስ የመነሻ ክፍያ /Minimum wage/ ይወሰናል፡፡ መነሻ የደመወዝ መጠን 1000.00 ብር እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ሐ- የጉልበት ሰራተኛ የቀን አበል አከፋፈል ወቅቱን የጠበቀና ከኑሮ ውድነቱ ጋር የተመጣጠነ መነሻ ክፍያ እንዲኖር ይደረጋል፡፡ በዚህም መሰረት መነሻ የቀን የጉልበት ሰራተኛ ደመወዝ እንደ አካባቢውና እንደስራው ሁኔታ የሚወሰን ሆኖ ከ 60.00 ብር ያላነሰ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

መ- ከመስሪያ ቤት ውጪ ለሚደረጉ የመንግስት ስራዎች የውሎ አበል፣ የጉርሻ ክፍያ፣ የነዳጅ አበል፣ የቤት አበል፣ የበረሀ አበል፣ የበአላትና የትርፍ ሰዓት ስራ ከመደበኛ ሰዓት ተጨማሪ ስራ ክፍያና አጠቃላይ የልዩ ልዩ ጥቅማጥቅም የአከፋፈል ስርዓት እንዲሻሻል ይደረጋል፡፡ በዚህም መሰረት ከወር ደሞዝ ጋር ተደምሮ የሚከፈለውን የገቢ ግብር አከፋፈል ስርዓት እንዲቀር ይደረጋል፡፡

ሠ- የመንግሥት የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች በወጪ መጋራት አሰራር ከመንግሥት የሚመደብላቸው የምግብ ፍጆታ ገንዘብ ከወቅቱ የኑሮ ውድነት ጋር የሚመጣጠን እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ረ- አትራፊ የሆኑና የመንግሥት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት (ቴሌ፣ መብራት ኃይል እና ውሃና ፍሳሽን የመሳሰሉ) ለአገልግሎታቸው የሚጠይቁት ክፍያ ከሕዝቡ የመግዛት አቅም ጋር የተመጣጠነ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ በተለይ ልዩ ትኩረት የሚሻውን በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኙትን የኅብረተሰብ ክፍሎች ከአቅማቸው ጋር የተገናዘበ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ሰ- የነዳጅ ዋጋ በዓለም ገበያ ከፍተኛ ጭማሪ በሚያሳይበት ወቅት መንግሥት ኅብረተሰቡን በጊዜያዊነት የሚደጉምበት አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡ የትራንስፖርት ዋጋን የሚቀንሱ ተመሳሳይ እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

ሸ- የኑሮ ውድነቱ እስኪረጋጋ ድረስ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ የሚገኘውን የኅብረተሰብ ክፍል ከፍተኛ ወጪ በሚጠይቁ የምግብ ፍጆታዎችና ሸቀጦች ላይ ከፍተኛ የግብርና የቀረጥ ቅነሳ ይደረጋል፡፡

ቀ- የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት የሚወሰዱ እርምጃዎች አርሶ አደሩን ህዝብ የሚጐዳ ውጤት እንዳያስከትሉ ለማድረግ የሚወሰዱት መፍትሄዎች የሸማቹን ህዝብ የመግዛት አቅም የሚያጠናክሩ እንጂ የአርሶ አደሩን ህዝብ የምርት ዋጋ በከፍተኛ መጠን የሚቀንሱ ወይም የሚያረክሱ በማይሆንበት አግባብ እንዲፈፀሙ ይደረጋል፡፡ መንግስት የተደረገው ቅናሽ በትክክል ተፈጻሚ መሆኑን የሚያረጋግጥ ጥብቅ የአሰራር ስልት ይከተላል፡፡

**2007 ዓ.ም**

በ▪ አብዛኛው ሕዝብ የሚጠቀምባቸው (የተዘጋጁና ያልተዘጋጁ) የምግብ ዓይነቶች ከተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ሙሉ በሙሉ ነጻ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

ተ▪ ከኑሮ ውድነት ጋር ተያያዥነት ባላቸው ሌሎች አገልግሎቶችና ሸቀጦች ላይ በአሁኑ ወቅት የሚከፈለው 15 በመቶ የተጨማሪ እሴት ታክስ (VAT) ወደ 7.5 በመቶ እንዲቀንስ ይደረጋል፡፡

ቸ▪ በማንኛውም እቃና አገልግሎት ላይ የሚታዩ የተደራራቢ የተጨማሪ እሴት ታክስ ክፍያዎች ሙሉ በሙሉ እንዲወገዱ ይደረጋል፡፡

ነ▪ ተገቢ ያልሆነ ትርፍ ለማግኘት ሲሉ የኑሮ ውድነቱን በሚያባብስ ተግባር ላይ በሚሰማሩ ነጋዴዎች ላይ መንግሥት ጥብቅ የቁጥጥር፣ የክትትልና የቅጣት እርምጃ እንዲወሰድ የሚያስች

አሠራር ይዘረጋል፡፡

ኘ▪ በግብርናው ዘርፍ በአነስተኛ ወጪ ከፍተኛ የምግብ እህል ምርት የሚገኝበት ስልት እንዲኖር ይደረጋል፡፡ የግብርና የምርት ግብአቶች ከቀረጥ ነጻ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

አ▪ መሬት አልባ ለሆነው የገበሬ ልጅ ልዩ ትኩረት በመስጠት ወደ ኢንዱስትሪ አገልግሎትና ምርትና ምርታማነት የሚገባበት ስትራቴጂ ይዘጋጃል፡፡

ከ▪ በመንግሥት የሚከናወኑ የልማት ስራዎች የገንዘብ ግሽበት በማያባብሱበት አግባብ እንዲፈፀሙ ይደረጋል፡፡ በአጠቃላይም ከአገሪቱ አጠቃላይ ምርት የማይመጣጠን የገንዘብ መጠን ወደ ገበያ የማይገባበት አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

ወ▪ በጥናት ላይ የተመሠረቱ የአጭር፣የመካከለኛና የረዥም ጊዜ የገንዘብና የፊሲካል ፓሊሲ ማሻሻያ እርምጃዎች እንዲወሰዱ ይደረጋል፡፡

በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የመንግስት የፋይናንስ ጉድለት በአማካይ ከ 3 በመቶ በታች እንዲሆን የሚያስችል አሰራር ተግባራዊ ይደረጋል፡፡ የመንግስትና የሕዝብን ገንዘብ የሚያስተዳድሩ የገንዘብ ተቋማትና የአክሲዮን ማህበራት አደረጃጀትና አሠራር የአገሪቱን የማክሮ ኢኮኖሚ ደህንነት በሚያስጠብቅና የገንዘብ ግሽበትን መቆጣጠር በሚያስችል መልኩ እንዲሆን ይደረጋል፡፡ የአመት ትርፋቸው ከ 30 ሺ ብር በታች የሆነ አነስተኛ ነጋዴዎች ትርፍ ግብር አሁን ካለው 30 በመቶ 15 በመቶ ዝቅ እንዲል ይደረጋል ፡፡

## 5.1.2- ከዚህ በላይ በተዘረዘሩትና የኑሮ ውድነትን ለማቃለል ተብለው በሚወሰዱ እርምጃዎች ምክንያት የሚፈጠረውን የመንግሥት ገቢ መቀነስ ለማካካስ የሚወሰዱ እርምጃዎች-

ሀ- እያንዳንዷን የሙስናና የብክነት ቀዳዳ የሚደፍን፣ የፖለቲካ ወገንተኝነትንና የዝምድና አሰራርን ወደ ዜሮ በሚጠጋ ከፍተኛ መጠን የሚቀንስ አሰራር በመዘርጋት የመንግስት ገቢ እንዲጨምር ይደረጋል፡፡

ለ- በአሁኑ ወቅት በዝቅተኛ ደረጃ ላይ የሚገኘው የመንግሥት ታክስ የመሰብሰብ አቅም በከፍተኛ መጠን እንዲጠናከር በማድረግና ሁሉም ገቢ ያለው የአገሪቱ ዜጋ ታክስ የመክፈል ግዴታውን በአግባቡ እንዲወጣ የሚያስችል አሰራር በመዘርጋት የመንግሥት የታክስ መሠረትና ገቢ በሚቀጥሉት 5 ዓመታት ቢያንስ በ 200% እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

ሐ- በተለያዩ የግብርና፣ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት የኢንቨስትመንት ዘርፍ ለሚሰማሩ ባለሃብቶች ምቹ ሁኔታን በመፍጠር የመንግሥትን የታክስ መሠረትና መጠን በማሻሻል የመንግስት ገቢ ለሚቀጥሉት አምስት አመታት ቢያንስ በ 500% እንዲጨምር ይደረጋል፡፡

መ- አገሪቱ በውስጥ ጉዳዮቿና ከጎረቤቶቿ ጋር ባላት ግንኙነት አስተማማኝና ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት እንድትፈጥር በማድረግ የመከላከያና የደህንነት ወጪ ለሚቀጥሉት አምስት አመታት በየአመቱ በ 10 በመቶ እንዲቀንስ ይደረጋል፡፡

ሠ-በውጭ አገር ነዋሪ የሆኑ ትውልደ ኢትዮጵያውያንና የውጭ ባለሀብቶችን በአገር ውስጥ መዋዕለ-ንዋያቸውን በከፍተኛ መጠን ጥቅም ላይ እንዲያውሉ የሚስችል ምቹ ሁኔታ በመፍጠር የውጭ ቀጥተኛ ኢንቨስትመንት (FDI) በሚቀጥሉት አምስት አመታት ቢያንስ በ 500% እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

ረ- አገሪቱ ውስጥ አስተማማኝ ሰላምና መረጋጋት በመፍጠር ለቱሪዝም ኢንድስትሪ ምቹ ሁኔታ የሚፈጥር የመሠረተ ልማት ግንባታ በከፍተኛ መጠን የቱሪስት መስህብ ባለባቸው አካባቢዎች በማስፋፋትና የአገሪቱን በጐ የቱሪዝም ገፅታ ለዓለም በማስተዋወቅ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት ከዘርፉ የሚገኘው ገቢ ቢያንስ በ 500% እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

ሰ- በአገሪቱ ከንግድና ከኢንቨስትመንት ጋር የተያያዙ ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዶች እንዲወገዱ በማድረግ፤ የባንኮች አሰራር ቀልጣፋ ዘመናዊና ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆን በማድረግ፤የአገሪቱን የግብይት ስርዓት ቀልጣፋና ዘመናዊ በማድረግ፤ የመንግስት ገቢ እንዲጨምር ይደረጋል፡፡

ሸ- በአንድ በኩል የአገሪቱን የኤክስፖርት ገበያ በማጠናከር፣ በሌላ በኩል ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚገቡ ሸቀጦችና የሚተኩ ምርቶች በአገር ውስጥ እንዲመረቱ የሚያስችል ከፍተኛ ጥረት በማድረግ በሚቀጥሉት አምስት ዓመታት የአገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ጉድለት በ 50% እንዲቀንስ ይደረጋል፡፡ በተለይም በታዳሽ ሃይልና በማዕድን መስክ የሚካሄደው ኢንቨስትመንት በከፍተኛ መጠን እንዲያድግ በማድረግ የአገሪቱ የውጭ ምንዛሪ ግኝት እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

ቀ- የአገሪቱን የሰብዓዊ መብት አያያዝ በማሻሻል፣ ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን በማጠናከርና የግልጽነትና የተጠያቂነት አሰራርን በማጠናከር በሚቀጥሉት አምስት አመታት አገሪቱ ከውጪ ድርጅቶችና መንግስታት የምታገኘው እርዳታና ብድር ቢያንስ በ 300% እንዲያድግ ይደረጋል፡፡

## 5.1.3- ሰፊ የስራ እድልን ለዜጎች ለመፍጠር የሚወሰዱ እርምጃዎች

የእያንዳንዱ ዜጋ የግል ፍላጐት እንዲሟላም ሆነ አገራዊ ኢኮኖሚ በዘላቂነት እንዲያድግ በአንድ አገር በቂ የስራ ዕድል መኖር አለበት፡፡ ኢዴፓ ለወጣቱ ትውልድ የተለየ ትኩረት የሚሰጥ ፓርቲ ከመሆኑ አንጻር አዳዲስ የስራ ዕድሎች ተፈጥረው ወጣቱ ትውልድ የአገሪቱ ኢኮኖሚ ዋና አንቀሳቃሽ ሞተር የመሆንን ድርሻ በአግባቡ እንዲወጣ ለማስቻል የስራ ፈጠራ ጉዳይ ልዩ ትኩረት የሚሰጠው ይሆናል፡፡

በአሁኑ ወቅት በአገራችን ምን ያህል የስራ አጥ ቁጥር እንዳለ በትክክል የሚያሳይ መረጃ የሌለ ቢሆንም አንዳንድ ቀደም ሲል የተካሄዱ ጥናቶች እንደሚያሳዩት ከገጠሩ የአገራችን ሕዝብ ውስጥ ከ 60 በመቶ በላይ፣ ከከተማው የአገራችን ሕዝብ ደግሞ ከ 35 በመቶ ያላነሰው ስራ አጥ እንደሆነ ይገመታል፡፡ ይህ ሁኔታ ሳይለወጥ ስለድህነት ቅነሳም ሆነ ስለ አጠቃላይ የኢኮኖሚ ዕድገት ማውራት ስለማይቻል ኢዴፓ ለመንግሥት ሥልጣን ቢበቃ ቀዳሚ ትኩረት ከሚሰጣቸው ዋና ዋና አንገብጋቢ ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የስራ ፈጠራ ይሆናል፡፡ በቂ አዳዲስ የስራ ዕድሎች እንዲፈጠሩም የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

ሀ- የስራ አጥ ቁጥሩን በሚመለከት በአገራችን በቂ መረጃ የሌለ ስለሆነ ችግሩን በአግባቡ ለመፍታት የሚያስችል ከእያንዳንዱ ቀበሌ ጀምሮ እስከ አገር አቀፍ ደረጃ በስራ ላይ የሚገኙና የማይገኙ ዜጐችን መረጃ ለማግኘት የሚያስችል ጥናት ይካሄዳል፡፡ ጥናቱን በቋሚነት የሚያካሂድ መንግሥታዊ ተቋም እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡

ለ- በመንግሥት የሚነደፉ የልማት ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች አዳዲስ የስራ ፈጠራ ተልዕኮን በሚያሳኩበት ደረጃ እንዲዘጋጁ ይደረጋል፡፡ ለማንኛውም የኢንቨስትመንት መስክ መንግሥት የሚሰጣቸው ማበረታቻዎች ለስራ ፈጠራና መስፋፋት ቅድሚያ ለሚሰጡት መስኮች እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ሐ- አዳዲስ የስራ ዕድል በመፍጠር ረገድ ከፍተኛውን ሚና ሊጫወቱ የሚችሉት የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፎች በመሆናቸው አገሪቱ የምትከተለው የኢኮኖሚ ስትራቴጂ ግብርና መር የኢኮኖሚ ስትራቴጂ መሆኑ ቀርቶ የግብርና፣ የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፉ የሚገባቸውን ተመጣጣኝ ትኩረት አግኝተው በሂደት የኢንዱስትሪና የአገልግሎት ዘርፉ የመሪነቱን ሚና የሚጨብጡበት የኢኮኖሚ ስትራቴጂ እንዲኖር ይደረጋል፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ ለስራ ፈጠራ መሠረት የሆኑት የአገሪቱ ትላልቅና አነስተኛ ከተሞች የሚገባቸውን ትኩረት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

መ- ከፍተኛ የስራ መስክ በመፍጠር ረገድ አነስተኛና ጥቃቅን የኢንዱስትሪ ዘርፎች ከፍተኛ ሚና ያላቸው ቢሆንም፣ እነዚህ አነስተኛ ጥቃቅን የኢንዱስትሪ ዘርፎች ዘላቂ ህልውና ሊኖራቸው የሚችለው ምርቶቻቸውን የሚቀበሏቸው ሌሎች ዘርፎች ሲኖሩ ስለሆነ ይህንን ሚና ሊጫወቱ የሚችሉ የመካከለኛና ከፍተኛ የኢንዱስትሪ ዘርፎችም ከፍተኛ ትኩረት አግኝተው እንዲስፋፉ ይደረጋል፡፡

ሠ- ለማንኛውም በግልም ሆነ በማኅበር ለሚከፈቱና ከ10 ሰው በላይ መቅጠር ለሚችሉ የአነስተኛና ጥቃቅን የኢንዱስትሪ ዘርፎች መንግሥት ፈቃድ የመስጠት፣ የማምረቻ ቦታ የማዘጋጀት፣ ገበያ የማፈላለግ፣ ሥልጠና የመስጠትና በአነስተኛ ወለድ ብድር የመስጠት እገዛዎችን የሚያደርግ ሲሆን በዚህ ረገድ መንግሥት የሚሰጠው ድጋፍ ከሙስናና ከፖለቲካ ወገንተኝነት ፈጽሞ በፀዳ ሁኔታ እንዲፈፀም ይደረጋል፡፡

ረ- መደበኛ ላልሆኑ የስራ መስኮችና ዜጎች በግል የስራ ፈጠራ የራሳቸው ቀጣሪ ለመሆን የሚያደርጉትን ጥረት መን

ሥት ድጋፍ የሚያደርግበት አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

ሰ- ኢትዮጵያን በመሰሉ ታዳጊ አገሮች የመሰረተ ልማት ግንባታ ሰፊ የስራ ዕድል የሚፈጥር መስክ በመሆኑ አሁን በበጐ ጅምር ላይ የሚገኘው የአገራችን የግንባታ እንቅስቃሴ ጉድለቶች ተሟልተው የበለጠ ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡

በአጠቃላይ ኢዴፓ ለሥልጣን ሲበቃ ለተከታታይ አምስት ዓመታት በአገር ደረጃ በየዓመቱ ከ1.5 ሚሊዮን ያላነሱ አዳዲስ የስራ ዕድሎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡፡

## 5.14- ረሃብን ለማስወገድና ድህነትን ለመቀነስ የሚወሰዱ እርምጃዎች

ከዚህ በላይ የጠቀስናቸው የኑሮ ውድነትን ለማቃለልና አዳዲስ የስራ እድሎችን ለመፍጠር የምንሰራቸው ስራዎች ረሃብን ለማስወገድና ድህነትን በወሳኝ መልኩ ለመቀነስ የሚያስችሉን ዋናዎቹ ተግባራት ቢሆኑም በተለይም ረሃብን የማስወገድ ስራ ይዋል ይደር ሳይባል ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ አንገብጋቢ አገራዊ ጉዳይ ነው፡፡ ሌሎች አካላት የሚያቀርቡትን መረጃ ለጊዜው ትተን በራሱ በመንግሥት መረጃ መሠረት በአገራችን በየዓመቱ በአማካኝ ከ3.5 ሚሊዮን እስከ 6 ሚሊዮን ሕዝብ ድረስ ለረሃብ አደጋ ይጋለጣል፡፡ ይህ ችግር ልዩና ቀዳሚ ትኩረት ተሰጥቶት በረሃብ የመጠቃት ችግር ከአገራችን ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ በጥቂት ዓመታት ውስጥ ሊወገድ ይገባል ብሎ ኢዴፓ ያምናል፡፡ ችግሩን ለማስወገድም የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

ሀ- የአርሶ አደሩ ሕዝብ የመሬት ይዞታ ብቻ ሳይሆን የባለቤትነት መብት ሙሉ በሙሉ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

ለ- አዳዲስና ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች በከፍተኛ መጠን ጥቅም ላይ እንዲውሉ ይደረጋል፡፡

ሐ- የህዝብና የክልል መንግስታትን ፈቃደኝነት መሠረት ያደረገ በክልሎች ውስጥና ክልል ዘለል ጭምር የሆነ የሰፈራ ፕሮግራም በስፋት ይካሄዳል፡፡

መ- በአገሪቱ የኢኮኖሚ መዋቅራዊ ሽግግር በመፍጠር ዜጎች ከእጅ ወደ አፍ ከሆነውና ለዘመናት ለውጥ ካላመጣው የግብርና የስራ መስክ በከፍተኛ ፍጥነት እየወጡ በስፋት እንዲስፋፋ በሚደረገው  የኢንዱስትሪና አገልግሎት ዘርፍ እንዲቀጠሩ ይደረጋል፡፡

ሠ- አርብቶ አደሩ ኅብረተሰብ ዘመናዊ የከብት እርባታ ሥርዓት ውስጥ እንዲገባ የሚደረግ ሲሆን ፍቃደኛነቱን መሠረት ባደረገ አሰራር በከፍተኛ ፍጥነት ኑሮው ወደ ቋሚ ሰፋሪነት እንዲለወጥ ይደረጋል፡፡

ረ- ከተደጋጋሚ የረሃብ አደጋ ለመዳን ወሳኙ ስራ የአገሪቱን ግብርና ከዝናብ ጥገኝነት ማውጣት ስለሆነ ከአነስተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የሚካሄድ የመስኖ ስራ በአገሪቱ የመሰረተ ልማት የግንባታ ስራ ውስጥ ቀዳሚውን ስፍራ እንዲይዝ ይደረጋል፡፡

ሰ- የአገሪቱን የሕዝብ ቁጥር ዕድገት ከአገሪቱ የኢኮኖሚ ዕድገት ጋር የተመጣጠነ የሚያደርጉ የልማት እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

ሸ- የአገሪቱ ግብርና ከጥራጥሬ ምርት በተጨማሪ በተለያዩ ለፍጆታና ለገበያ በሚውሉ የእንሰሳት፣ የአትክልትና ፍራፍሬ ምርቶች እንዲያተኩር ይደረጋል፡፡

ቀ- የሕዝቡ የአመጋገብ ሥርዓት እንዲሻሻል፣ ብክነትን ማስወገድና የቁጠባ ባህሉ እንዲዳብር የሚያደርጉ የግንዛቤ ማስጨበጥና የማስተማር እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

በ- ረሃብን ለማስወገድና ድህነትን ለመቀነስ በአገሪቱ የሚከናወኑ ተግባራት የሴቶችን ሁለንተናዊ አቅም በማጐልበትና የአካል ጉዳተኞች ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ አቅም በማጐልበት ረገድ ልዩ ትኩረት የሚሰጡ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

ተ- ዘመናዊና ሰፋፊ እርሻዎችን ለማልማት ለሚችሉ ባለሀብቶች መንግስት የተለያዩ ማበረታቻዎችን በመስጠት ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ይደረጋል፡፡ በመንግስት እጅ የሚገኙና ምርት ማምረት ያቆሙ ሰፋፊ እርሻዎች በግል ባለሃብቶች እንዲያዙ ይደረጋል፡፡

ቸ- በአጠቃላይ ድህነትን በወሳኝነት ለመቀነስ የሚያስችሉና የምዕተ ዓመቱን  የልማት ግቦች በአገራችን ስኬታማ እንዲሆኑ የሚያስችሉ ጥረቶች ይደረጋሉ፡፡

እነዚህን ተግባራት በብቃት በማከናወን በመጭዎቹ 5 ዓመታት ውስጥ አገሪቱ በአገር ደረጃ በምግብ እህል ምርት እራሷን ችላ ከውጭ ተመጽዋችነት ነጻ እንድትወጣ፤ በ10 ዓመታት ውስጥ ደግሞ እያንዳንዱ ቤተሰብና ዜጋ ከረሃብ አደጋ ነጻ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

## 5.1.5- በኢኮኖሚ ረገድ ትኩረት የሚሰጣቸው ሌሎች ልዩ ልዩ ጉዳዮች

ሀ- ለሙስና ተጋላጭ ናቸው በሚባሉ እንደ ጉምሩክ፣ አገር ውስጥ ገቢ፣ ፍርድ ቤት፣ አቃቢ ህግ፣ፖሊስ፣ ደህንነትና ኢሚግሬሽን፣ ጸረ ሙስና ኮሚሽን፣ መንገድ ትራንስፖርት፣ ደረጃ መዳቢና ማዘጋጃ ቤትን የመሳሰሉ የመንግስት መስሪያ ቤቶች ውስጥ ተቀጥረው የሚሰሩ ሰራተኞች ከሌላው የመንግስት ሰራተኛ በተለየ በልዩ የስነ-ምግባር መመዘኛና ብቃት ተመርጠው የሚቀጠሩና ለኑሯቸው በቂ የሆነ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም እንዲያገኙ የሙስና ወንጀል ፈጽመው ሲገኙ ግን ከባድ ቅጣት እንዲጣልባቸው የሚያስችል ልዩ የህግ ድንጋጌ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

ለ- የአገሪቱን የውጭ ምንዛሬ ግኝት በማጠናከር፣ ከፍተኛ የስራ እድል ለዜጎች በመፍጠርና የምግብ ምርትን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ሚና ላላቸው የኢንቨስትመንት ዘርፎች ልዩ ማበረታቻ እንዲሰጥ ይደረጋል፡፡ ለእነዚህ የኢንቨስትመንት ዘርፎች የሚሰጠው ማበረታቻ መሬት በነጻ የመስጠት፣ ከውጭ ወደ አገር ውስጥ የሚያስገቧቸውን ማሽነሪዎች ከቀረጥ ነጻ እንዲያስገቡ የመፍቀድና በሚያቀርቡት የፕሮጀክት አዋጭነት መመዘኛ የባንክ ብድር እንዲያገኙ ማድረግን የሚያካትት ይሆናል፡፡

ሐ- በግሉ ዘርፍና በገበያ ውድድር የሚሸፈኑ የመንግሥት የልማት ድርጅቶች በፍጥነት ወደ ግል ይዞታነት እንዲዛወሩ ይደረጋል፡፡ በአንድ ጊዜ ወደ ግል ይዞታነት ሊዛወሩ የማይችሉ አንዳንድ የመንግሥት የልማት ድርጅቶችም ከፊል ስራቸውና አገልግሎታቸው ቀስ በቀስ ወደ ግል ይዞታነት የሚዛወርበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

መ- በአገሪቱ የነፃ ገበያ ስርዓት ውስጥ የመንግስት ድርሻና ጣልቃ ገብነት እስከምን ድረስ እንደሚሆን በማያሻማ መልኩ ግልፅ በሆነ ሁኔታ በህግ እንዲደነገግና እንዲታወቅ ይደረጋል፡፡ በተለይም በአሁኑ ወቅት የአገሪቱ የመከላከያ መዋቅር በኢኮኖሚው ውስጥ እያደረገው ያለው ገደብ የለሽ ተሳትፎ በህግ እንዲገደብ ይደረጋል፡፡

ሠ- ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ቀጥተኛም ሆነ ተዘዋዋሪ ግንኙነት ያላቸው የንግድ ድርጅቶች በስም ብቻ ሳይሆን በተግባር ወደ ሕዝብ የጋራ ይዞታነት እንዲዛወሩ ይደረጋል፡፡

ረ- በኪራይ ቤቶች አስተዳደርና በቀበሌዎች ባለቤትነት የታያዙና በመልሶ መልማት የማይፈርሱ የኪራይ ቤቶች ማህበራዊ ቀውስ በማያስከትል መንገድ ወደ ግል ይዞታነት እንዲዛወሩ ይደረጋል፡፡ በማዘወሩ ሂደት በቤቶቹ ውስጥ ነዋሪ የሆኑ ሰዎች በቅድሚያ ክፍያ ወይም በረጅም ጊዜ ብድር ቤቶቹን ቅድሚያ አግኝተው እንዲገዙ ይደረጋል፡፡

ሰ- በደርግ ስርአት ንብረታቸው ያለ አግባብ የተወረሰባቸው ዜጎች የተጓደለባቸውን ፍትህ በሚያካክስ መልኩና የአገሪቱን አቅም በአገናዘበ መጠን የካሳ ክፍያ ከመንግስት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ሸ- የውጭ ባለሃብቶች (በተለይም ትውልደ ኢትዮጵያውያን) ወደ አገሪቱ ገብተው መዋዕለ ንዋያቸውን እንዲያፈሱ የሚያስችል ሰፊ ጥረትና አገዛ ይደረጋል፡፡

**2007 ዓ.ም**

ቀ- በአገሪቱ እየተካሄደ ያለው የመሠረተ ልማት ግንባታ ሂደት በጥራትና በስፋት ለሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች እንዲዳረስ በሚያስችል መጠን ተጠናክሮ እንዲቀጥል የሚደረግ ሲሆን፤ በዘርፉ ውስጥ የአገር ውስጥ ተቋራጮች አቅማቸው አድጎ የጐላ ድርሻ እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

በ- በገጠሩ የአገራችን አካባቢ በተበታተነ ሁኔታ እየኖረ የሚገኘው ህዝብ በአንድ አካባቢ እየተሰባሰበ መኖር እስካልቻለ ድረስ ለገጠሩ ህዝብ የመሰረተ ልማት አገልግሎትን በብቃት ማዳረስ ስለማይቻል በህዝቡ ፈቃደኝነትና በበቂ ጥናት የተደገፈ የመንደር ማሰባሰብ (vilegization) ስራ እንዲጀመር ይደረጋል፡፡

ተ- የአገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ግኝት ለሚያሰፉና አንጻራዊ ጠቀሜታቸው (comparative advantage) ከፍተኛ ለሆነ የኢኮኖሚ ዘርፎች ልዩ ትኩረትና ማበረታቻ ይሰጣል፡፡

ቸ- በአገሪቱ ዜጎች መካከል ፍትሃዊ የገቢ ስርጭት እንዲኖርና የዜጎችን አመታዊ የነፍስ ወከፍ ገቢ የሚያሳድጉ የተለያዩ ፖሊሲዎች ተግባራዊ ይደረጋሉ፡፡

ኀ- በአገሪቱ አጠቃላይ የንግድና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴ ውስጥ በመረጃ አሰጣጥ፣ በግብርና ቀረጥ አተማመን፣ በመሠረተ ልማት አቅርቦት፣ በውጭ ምንዛሪ ፈቃድ፣ በብድር አሰጣጥ፣ በፈቃድ አሰጣጥና በጨረታ አፈጻጸም ዙሪያ የሚፈጸሙ ከማንኛውም ወገንተኝነት ጋር የተያያዙ አድሏዊ አሰራሮች እንዲወገዱ የሚያስችል የአሰራር ስርዓት ይዘረጋል፡፡

## 5.2- በማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ የሚወሰዱ እርምጃዎች

### 5.2.1- የትምህርት አገልግሎትን በጥራት ለማዳረስ የሚወሰዱ እርምጃዎች

ሀ- የአገሪቱ የትምህርት ሥርዓትና መዋቅር ሙሉ በሙሉ ከማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ተጽዕኖና ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡

ለ- የአገሪቱ የትምህርት ሥርዓት አወቃቀር አሁን በስራ ላይ ካለው 8+2+2 አወቃቀር 6+2+4 አወቃቀር እንዲቀየር ይደረጋል፡፡ ማለትም ከ 1-6 የመጀመሪያ ደረጃ ከ 7-8 የመለስተኛ ደረጃ ከ 9-12 የከፍተኛ 2 ኛ ደረጃ አወቃቀር እንዲቀየር ይደረጋል፡፡

ሐ- ከአንድ እስከ አስራ ሁለተኛ ክፍል ባለው የትምህርት እርከን ማንኛውም ተማሪ ያለገደብ ደጋግሞ የመፈተንና ውጤቱን የማሻሻል መብት እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

መ-እያንዳንዱ ተማሪ የአንደኛ ደረጃ ትምህርትን በአፍ መፍቻ ቋንቋው የመማር መብቱ እንደተጠበቀ ሆኖ የትምህርት ሥርዓቱ በአገር አቀፍ ደረጃ ወጥ አሰራር እንዲኖረው ይደረጋል፡፡

ሠ- ለሴት ልጆች የትምህርት ተሳትፎና በተለያዩ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጫናዎች ምክንያት የጀመሩትን ትምህርት ለማቋረጥ የሚገደዱ ተማሪዎች ጉዳይ ልዩ ትኩረት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

ረ- የከፍተኛ ትምህርት ተማሪዎች እንደ ትምህርቱ ዓይነትና ባህሪ በአማካይ ለዲፕሎማ ከ 2-3 ዓመታት፣ ለመጀመሪያ ዲግሪ ከ 4-5 ዓመታት፣ ትምህርታቸውን በጥራትና በስክነት እንዲከታተሉ ይደረጋል፡፡

ሰ- የቴክኒክና የሙያ ትምህርትና ስልጠና ጥራቱ ይበልጥ ተሻሽሎ እንዲስፋፋ ይደረጋል፡፡ ማዕከላቱ ተከታታይ የጥራት ምዘናና የማያቋርጥ የፈጠራ ምርምር የሚካሄድባቸው እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

ሸ- ከአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት እስከ ዩንቨርሲቲ ደረጃ ተቀጥረው የሚሰሩ መምህራን በስፋትና በጥራት እንዲሰለጥኑ ይደረጋል፡፡ ለመምህራኑ ኑሮና ክብር በሚመጥን ሁኔታ ከፍተኛ የደመወዝ ጭማሪና ጥቅማጥቅም እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ቀ- በአጠቃላይ የአገሪቱ የትምህርት ሥርዓት ከይድረስ-ይድረስ የዘመቻ አሰራር ወጥቶ በጥራትና በብቃት እንዲመራ ይደረጋል፡፡

በ- የአገሪቱ ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ከማንኛውም የፖለቲካ ጣልቃ ገብነት ነጻ ሆነው በሕዝቡ መሠረታዊ ችግሮች ላይ ያተኮረ ጥናትና ምርምር የሚካሄድባቸው ጥራት ባለው የሰው ኃይልና ቁሳቁስ የተደራጁ ተቋማት እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

ተ- የአገር ውስጥ የከፍተኛ ትምህርት ዕድሎችና አገሪቱ ከተለያዩ የውጭ ድርጅቶችና መንግሥታት የምታገኛቸው የውጭ ትምህርት ዕድሎች ከፖለቲካ ወገንተኛነትና ከማናቸውም ዓይነት አድሎ ነጻ በሆነ መንገድ ለዜጎች እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

ቸ- ለግል የትምህርት ተቋማት የተለያዩ ማበረታቻዎች የሚሰጡ ሲሆን፤ በዚያው መጠን የትምህርት ጥራትን በሚመለከት ከፍተኛ ክትትልና ቁጥጥር እንዲደረግባቸው የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፡፡

የትምህርት በጀት አሁን ከሚገኝበት ደረጃ ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በየዓመቱ ቢያንስ 2 0 በመቶ እንዲጨምር ይደረጋል፡፡

## 5.2.2- የጤና አገልግሎትን በስፋትና በጥራት ለማዳረስ የሚወሰዱ እርምጃዎች

ሀ- የኢዴፓ የጤና ፖሊሲ በሽታን አስቀድሞ በመከላከል ዙሪያ የሚያተኩር ሲሆን፣ ከጤና ጋር በተያያዘ ልዩና ቀዳሚ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች ዜጎች በተለይም ህጻናት ተመጣጣኝ ምግብ እንዲያገኙ ማድረግና፣ ሁሉም የአገሪቱ ዜጎች የመጸዳጃ ቤትና ንጹህ የመጠጥ ውሃ እንዲያገኙ ማድረግ ይሆናል፡፡

ለ- በአገሪቱ በሰራተኛው ሃይል ላይ ከፍተኛ ጉዳት እያደረሱ የሚገኙ እንደ ኤች አይ ቪ ኤድስና ወባን የመሳሰሉ በሽታዎችን አስቀድሞ የመከላከል ስራ ልዩና ቀጣይ ትኩረት የሚሰጠው ሲሆን፣ የኤች አይ ቪ ኤድስ ህሙማን ባሉበት አካባቢ መድሃኒት በነጻ እንዲያገኙና በቂ ምግብ የማግኘት ችግር ያለባቸው የኤድስ ህሙማንም የመንግሥት ድጋፍ የሚያገኙበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

ሐ- የጤና ተቋማትን በሁሉም የአገሪቱ አካባቢዎች የማዳረሱ አስፈላጊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋማቱ በመድሃኒት፣ በባለሞያና በቁሳቁስ የተሟሉ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

መ- ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ደረጃ የሚገኙ የጤና ባለሞያዎች ቀጣይነትና ተከታታይነት ባለው መልኩ በስፋትና በጥራት እንዲሰለጥኑ ይደረጋል፡፡ ለጤና ባለሞያዎች ኑሮና ክብር በሚመጥን ሁኔታ ከፍተኛ የደመወዝ ጭማሪና ጥቅማጥቅም እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ሠ- በጤና መስክ ለሚሰማሩ የግል ባለሃብቶች መንግሥት የተለያዩ ማበረታቻዎችን የሚያደርግ ሲሆን፣ በአገልግሎት አሰጣጣቸው ላይ ከፍተኛ ክትትልና ቁጥጥር ይደረጋል፡፡ በጤና ጉዳይ የሚፈጸም ማናቸውም ወንጀል ላይ ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትል አሰራርና ሕግ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

ረ- በአዲስ አበባ ከተማና በዋና ዋና የክልል ከተሞች ተጨማሪ ከፍተኛ ሪፈራል ሆስፒታሎች እንዲከፈቱ ይደረጋል፡፡

ሰ- በመላ አገሪቱ የመድኃኒት አቅርቦትና ስርጭት በተመጣጠነ ሁኔታ በባለሞያ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ የመድኃኒት አቅርቦትና ስርጭት የገጠሩን ህብረተሰብ ማዕከል ባደረገ ሁኔታ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ የመድኃኒት ዋጋም የህብረተሰቡን የመግዛት አቅም ባገናዘበ ሁኔታ እንዲከናወን ይደረጋል፡፡ የቁጥጥርና ክትትል መመሪያም እንዲዘጋጅ ይደረጋል፡፡

የጤና በጀት አሁን ከሚገኝበት ደረጃ ለሚቀጥሉት አምስት ዓመታት በየዓመቱ ቢያንስ 20 በመቶ እንዲጨምር ይደረጋል፡፡

## 5.2.3- በመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ የሚታዩ ቢሮክራሲያዊ ውጣ ውረዶችን፣ ሙስናንና ብክነትን ለማስወገድ፣ በአጠቃላይም የመልካም አስተዳደር ችግሮችን ለመፍታት የሚወሰዱ እርምጃዎች

ሀ- የአገሪቱ የፍትህ ተቋማትና አሰራር ሙሉ በሙሉ ከፖለቲካ ተጽዕኖና ጣልቃ ገብነት ነጻ በሆነና የሞያ ብቃትን፣ መልካም ሥነ-ምግባርንና ነጻ አመለካከትን መሠረት ባደረገ አሰራር እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡

ለ- በፍርድ ቤትና ፍትህ ነክ በሆኑ የፖሊስ፣ የአቃቤ ሕግ፣ የፀረ-ሙስና፣ የእንባ ጠባቂና የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ተቋማት የሚሰሩ ባለሞያዎች በልዩ የደመወዝ ስኬል የሚቀጠሩና ለኑሮአቸው በቂ የሆነ ደመወዝና ጥቅማጥቅም የሚያገኙ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡ በነዚህ ባለሙያዎችና ተቋማት ለሚፈጸም ወንጀል ከባድ ቅጣት የሚያስከትል አሰራርና ሕግ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

ሐ- ሁሉም የፍትህ ተቋማት ግልጽነት፣ ዘመናዊነት፣ ቅልጥፍናና ለሕዝቡ ተደራሽነት ባለው አሰራር እንዲደራጁ ይደረጋል፡፡

መ- መንግሥት ለዜጐች የሚሰጣቸው ማናቸውም ዓይነት አገልግሎቶች በተለይም ከመሠረተ ልማት ጥያቄ፣ ከንግድ ፈቃድ አሰጣጥ፣ ከታክስና ግብር አከፋፈል፣ ከግንባታ ፈቃድና ከመረጃ ጥያቄ ጋር የተያያዙ የተለያዩ አገልግሎቶች ያለ ውጣ ውረድ ለህዝቡ ቅርበት ባለው ግልጽ፣ ዘመናዊና ፈጣን በሆነ አሰራር እንዲሰጡ ይደረጋል፡፡

ሠ- ከሚኒስትር፣ ከምክትል ሚኒስትርና ከኮሚሽነር በእነዚህ ደረጃ ከሚገኙ የሥልጣን እርከኖች በታች የሆኑ የመንግሥት መስሪያ ቤት ኃላፊነቶች በሙሉ ከፖለቲካ ወገንተኝነት ነጻ በሆነ መንገድ በትምህርት፣ በሞያ፣ በሥነ-ምግባርና በአገልግሎት ልምድ ብቃት በውድድር የሚያዙ እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

ረ- በአሁኑ ወቅት እየተካሄዱ የሚገኙ የስራ ሂደት ማስተካከያ እርምጃ ጉድለቶቻቸው ስህተቶቻቸው ታርመው ተጠናክረው እንዲቀጥሉ ይደረጋል፡፡ ሂደቱ ሙሉ በሙሉ ከፖለቲካ ወገንተኝነትና ተጽዕኖ ነጻ በሆነ ግልጽ አሰራር እንዲካሄድ ይደረጋል፡፡

## 5.2.4- የመኖሪያ ቤት ችግርን ለመፍታት የሚወሰዱ እርምጃዎች

ሀ-በአሁኑ ወቅት በመንግሥት እየተካሄደ የሚገኘው የኮንደምኒየም ቤቶች

ንባታ ጉድለቶቹና ድክመቶቹ ታርመው ተጠናክሮ እንዲቀጥል ይደረጋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በአዲስ አበባና በተለያዩ የአገሪቱ ከተሞች የኮንዶምኒየም ቤት በእጣ ለማግኘት ተመዝግበው የሚገኙ ዜጐች በመጭዎቹ አምስት ዓመታት የቤት ባለቤት ለመሆን በሚችሉበት መጠን አዳዲስ ቤቶች ይገነባሉ፡፡

ለ- የመኖሪያ ቤት የመግዛት አቅም ወይም ፍላጐት የሌላቸው ዜጐች ከ 300 ብር ባልበለጠ ገንዘብ ተከራይተው ሊኖሩባቸው የሚችሉ አነስተኛ መጠን ያላቸው ቤቶች በስፋት እንዲገነቡ አመቺ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ይደረጋል፡፡

ሐ- የመኖሪያ ቤቶችን በዝቅተኛ ዋጋ እየገነቡ በተመጣጣኝ ዋጋ የመሸጥ ወይም የማከራየት ስራ በመንግሥት ብቻ ሳይሆን በግል ባለሃብቶችም የሚካሄድበት ምቹ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ግለሰቦች መሬትና የተለያዩ ማበረታቻዎች ከመንግሥት እየተሰጣቸው አስቀድሞ ከመንግሥት ጋር በሚደረግ ድርድር በሚወሰን ተመጣጣኝ ዋጋ ቤቶችን እየሰሩ ለቤት ፈላጊ ዜጐች እንዲሸጡና እንዲያከራዩ የሚያስችል አሰራር በስፋት እንዲኖር ይደረጋል፡፡

መ- ከመንግሥት የመኖሪያ ቤት ለመግዛትና ለመከራየት ሴቶችና አካል ጉዳተኞች ቅድሚያ የሚሰጣቸው መሆናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ባለትዳር መሆንና የልጆች ብዛት ተጨማሪ መመዘኛ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

# 2007 ዓ.ም

## 5.2.5የተፈጥሮ ሐብትና የአካባቢ ጥበቃን በተመለከተ የሚወሰዱ እርምጃዎች

ሀ- ከአካባቢ ጥበቃ አኳያ የኢዴፓ የመጀመሪያ ትኩረት በጥናትና በእቅድ ላይ የተመሰረተና ዘላቂነት ያለው የደን ልማት ስራ በአገሪቱ እንዲኖር ማድረግ ይሆናል፡፡

ለ- እያንዳንዱ በመንግሥትም ሆነ በግል የሚካሄድ የልማት ፕሮጀክት ከአካባቢ ደህንነት አኳያ የሚኖረው ተጽዕኖ በጥንቃቄ እንዲመዘን የሚያስችል አሰራር ይዘረጋል፡፡

ሐ- በአሁኑ ወቅት እየተሰራ የሚገኘውን የታዳሽ የኤሌትሪክ ሃይል የማመንጨት ስራ የበለጠ አጠናክሮ በመቀጠል የአገሪቱ የሃይል አቅርቦት በከፍተኛ ፍጥነት ከማገዶ እንጨትና ከነዳጅ የጸዳ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

መ-በአገሪቱ የሚገኙ በነዳጅ የሚሰሩ የተለያዩ ጄኔሬተሮችና ማሽነሪዎች በኤሌክትሪክ ኃይል የሚተኩበት ሁኔታ ይመቻቻል፡፡

ሠ- ከ 1 0 ዓመት በፊት የተመረቱ ተሽከርካሪዎች ወደ አገር ውስጥ እንዳይገቡ የሚከለከል ሲሆን አዳዲስ መኪናዎች ወደ አገር ውስጥ እንዲገቡ የሚያበረታታ የቀረጥ ቅናሽ ይደረጋል፡፡

ረ- የድምጽ ብክለትን ጨምሮ ማናቸውንም ዓይነት የአካባቢ ብከላ ለመከላከል ወይም በከፍተኛ መጠን ለመቀነስ የሚያስችል ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተገናዘበ ሕግና አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

## 5.2.6- ልዩ ልዩ ማህበራዊ ጉዳዮች

ሀ- በዋና ዋና ከተሞች በእያንዳንዱ ክፍለ ከተማ አንድ መለስተኛ ሁሉን አቀፍ የስፖርት ማዘውተሪያ ስታዲዮም፣ በገጠር ቢያንስ በእያንዳንዱ ወረዳ አንድ አነስተኛ ሁሉን አቀፍ የስፖርት ማዘውተሪያ እንዲገነባ ይደረጋል፡፡

ለ- በእያንዳንዱ የአገሪቱ ቀበሌዎች አንድ የመጽሀፍት ቤትና የኢንፎርሜሽን ማዕከል፣የህጻናትና የወጣቶች የመዝናኛ ማዕከል እንዲደራጅ ይደረጋል፡፡ በዚህ ተግባር ላይ ለሚሳተፉ የግል ባለሃብቶች የተለያዩ ማበረታቻዎች ይደረጋሉ፡፡

ሐ- እድሜያቸው ከ 18 ዓመት በታች ለሆኑ ታዳጊ ወጣቶች ጫትን ጨምሮ ማንኛውንም አይነት አደንዛዥ ዕጽ፣ትምባሆና የአልኮል መጠጥ መሸጥን በጥብቅ የሚከለክልና ከፍተኛ ቅጣት የሚያስከትል ህግ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

መ- የሁሉም የሀገሪቱ የከተሞች ፕላን በቂ የህዝብ የመናፈሻ ቦታዎችን፣ የቆሻሻ ማስወገጃ ስፍራዎችን፣ የቄራ አገልግሎትን፣ የገበያ ቦታዎችን፣ የስፖርት ማዘውተሪያ ቦታዎችን፣ የእግረኛ መንገዶችንና የአካል ጉዳተኞች መተላለፊያ መንገዶችን በበቂ ሁኔታ ያካተተና ያገናዘበ እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ሠ- መንግስት ለአገሪቱ በጎ ባህሎች መጠበቅና ለስነ-ጥበብ መስፋፋት ልዩ ትኩረት ይሰጣል፡፡ የአገር ውስጥ ፊልሞች፣ ቲያትሮች፣ ሙዚቃዎች፣ ስዕሎች፣ ቅርጻ ቅርጾችና በአጠቃላይ የህትመት ውጤቶች እንዲዳብሩና እንዲስፋፉ መንግስት ከፍተኛ እገዛ የሚያደርግበት አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

ረ-እየተባባሰ የመጣውና የዜጐችን ህይወት እየቀጠፈ የሚገኘውን የመኪና አደጋ መንግስት ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ዘመናዊ የትራፊክ ማኔጅመንት እንዲዘረጋ ይደረጋል፡፡

## 5.3. በፖለቲካ ጉዳዮች ዙሪያ የሚወሰዱ እርምጃዎች

በፖለቲካ ረገድ የኢዴፓ ቀዳሚ አጀንዳ በአሁኑ ወቅት የሚታየው አንጻራዊ ሰላምና መረጋጋት እንደተጠበቀ ሆኖ የአገሪቱ ሰላምና መረጋጋት ወደኋላ ሊመለስ በማይችልበት ደረጃ አስተማማኝና ዘላቂ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ይህንንም ዓላማ ለማሳካት በአንድ በኩል በአገር ውስጥ ጠንካራ ብሔራዊ መግባባት በመፍጠር የፖለቲካ መረጋጋትን ማምጣት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ከጐረቤት አገሮች ጋር የጋራ ጥቅምን መሠረት ያደረገ ጤናማ ግንኙነት መፍጠር የፓርቲው ቀዳሚ ተግባራት ይሆናሉ፡፡ በአገሪቱ አስተማማኝና ዘላቂ ሰላምና መረጋጋት እንዲመጣ የሚከተሉት እርምጃዎች ይወሰዳሉ፡፡

ሀ- የሕግ የበላይነት በወረቀት ላይ ብቻ ሳይሆን በተግባር በአገሪቱ እንዲከበር፣ የዜጐች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሙሉ በሙሉ በተግባር እንዲከበሩ ይደረጋል፡፡

ለ- የመንግስት መገናኛ ብዙሃን ከማንኛውም የፖለቲካ ድርጅት ተጽዕኖ ነጻ በሆነ ገለልተኛ ቦርድ እንዲተዳደሩ ይደረጋል፡፡ በሚቀጥሉት አምስት አመታት ከ 5 ያላነሱ የመካከለኛና የአጭር ሞገድ ስርጭት ያላቸው የግል ሬድዮ ጣብያዎች እንዲኖሩ የሚያስችል ጥረት ይደረጋል፡፡ የጋዜጠኝነት ስነ-ምግባርን አክብረው የሚሰሩ የግል ፕሬሶች የህዝብ ተደራሽነታቸው የበለጠ እንዲጠናከር የሚያስችል ማበረታቻ ይደረግላቸዋል፡፡

ሐ- የአገሪቱን ህጎች አክብረው በሰላማዊ መንገድ ለሚንቀሳቀሱ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሙያ ማህበራትና የበጎ አድራጎት ድርጅቶች በነጻነት መደረጀትና መንቀሳቀስ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ በአገሪቱ እንዲፈጠር መንግስት ከፍተኛ እገዛ ያደርጋል፡፡

መ- በአገሪቱ የትጥቅ ትግል የሚያካሂዱና በስደት የሚገኙ የፖለቲካ ኃይሎች ወደ አገሪቱ እንዲገቡና ሰላማዊ የፖለቲካ መድረኩን እንዲቀላቀሉ ጥሪ ይደረግላቸዋል፡፡ ጥሪውን በተቀበሉ የፖለቲካ ኃይሎች መካከል ብሔራዊ እርቅ እንዲፈጠር የሚያስችል የእርቀ ሰላም መድረክ ይፈጠራል፡፡

ሠ- በአገሪቱ በስራ ላይ የሚገኙ የዴሞክራሲ ተቋማትና ሕግጋቶች በሕዝብ ተሳትፎና ውሳኔ ነፃ ገለልተኛና ብቁ መሆን የሚያስችላቸው ማሻሻያ እንዲደረግባቸው ይደረጋል፡፡

ረ- በአገሪቱ ከፖለቲካ ጋር በተያያዘ ምክንያት በማረሚያ ቤት የሚገኙ ዜጎች ሙሉ ምህረት እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

## 5.3.1 ለአገሪቱ አንድነት መጠናከርና ለተሻለ የኢኮኖሚ እድገት የሚያበቁ ህገ-መንግስታዊ ማሻሻያዎች ማድረግ

የአገሪቱ ሕገ-መንግሥት በሚፈቅደው መሠረት በሕዝብ ውሳኔ ሊሻሻሉ ከሚገባቸው ሕገ-መንግሥታዊ ጉዳዮች ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ይሆናሉ፡፡

ሀ- በኢትዮጵያ ሕገ-መንግሥት ቡድኖች ሳይሆኑ እያንዳንዱ የአገሪቱ ዜጋ የአገሪቱ ባለቤት መሆኑ እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡

ለ- የፌዴሬሽን ምክር ቤት እንደ ሌሎች አገሮች ሴኔቶች ሕግ የማውጣት ሥልጣን እንዲኖረውና የአገሪቱን አንድነት የሚያጠናክር ተዋጽዖና አሰራር እንዲኖርው ይደረጋል፡፡

ሐ- በፌዴሬሽን ምክር ቤት ክልሎች በህዝብ ተመራጭ በሆኑ ተወካዮቻቸው አማካኝነት ተመጣጣኝ ውክልና እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

መ- ህገ-መንግሥትን የመተርጐም መብት የፌዴሬሽን ምክር ቤት መሆኑ ቀርቶ እራሱን የቻለና በነጻነት የሚሰራ ሕገ-መንግሥታዊ ፍርድ ቤት እንዲቋቋም ይደረጋል፡፡

ሠ- የአገሪቱ ጠቅላይ ሚኒስትር ከሁለት ጊዜ በላይ በድጋሚ እንዳይመረጥ የሚያስችል ገደብ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

ረ- በቆዳ ስፋታቸውና በህዝብ ብዛታቸው ተመጣጣኝነት ያላቸው ክልሎች እንዲኖሩ ይደረጋል፡፡ ክልሎቹን ለማዋቀር የህዝቡ አብሮ የመኖር ታሪካዊ ትስስር፣ ብሄረሰባዊ ማንነትና ቋንቋ፣ አስተዳደራዊ አመችነት፣ ኢኮኖሚያዊ አመችነት፣ የቆዳ ስፋትና የሕዝብ ብዛት እንደየ አካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ በጋራና በተናጠል በመስፈርትነት ጥቅም ላይ ይውላሉ፡፡

ሰ- ክልሎች በታክስ አሰባሰብና በተፈጥሮ ሃብት ባለቤትነትና አስተዳደር ትርጉም ያለው መብት እንዲኖራቸው ይደረጋል፡፡

ሸ- ክልሎች ከማንኛውም ቀጥተኛና ቀጥተኛ ያልሆነ ተጽዕኖ ነጻ ሆነው የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው የመወሰን የማይሸራረፍ መብት ይኖራቸዋል፡፡ ነገር ግን በመላው የዓለም አገሮች እንደሚታየው ሁሉ የኢትዮጵያም ሕገ-መንግሥት የመገንጠል መብትን የማያካትት እንዲሆን ይደረጋል፡፡

ቀ-የመሬት ባለቤትነት ጉዳይ ሕገ-መንግሥታዊ ድንጋጌ መሆኑ እንዲቀር ይደረጋል፡፡ መሬት እንደ የአካባቢው ሁኔታ በሦስት ዓይነት አማራጭ ስሪት ማለትም በግል፣ በጋራና በመንግሥት በባለቤትነት የሚያዝበት አማራጭ እንዲኖር ይደረጋል፡፡ በአሁኑ ወቅት በአርሶ አደሩ ይዞታ ስር የሚገኙ የገጠር መሬቶችና በከተሞች ዜጐች መኖሪያ ቤት ወይም ሌላ ግንባታ ያካሄዱባቸው መሬቶች ከተሟላ የባለቤትነት መብት ጋር የግል ንብረት እንዲሆኑ ይደረጋል፡፡

በ- ሕገ-መንግሥቱን የማሻሻል ዕድል አሁን ካለው ግትር አሰራር ወጥቶ በተወካዮች ምክር ቤትና በፌዴሬሽን ምክር ቤት 2/3 ድምፅና ከክልል መንግስታት 3/4 በአብላጫ ድምፅ ሲደግፉት የሚሻሻልበት አሰራር እንዲኖር ይደረጋል፡፡

## 5.4 የውጭ ጉዳይን በተመለከተ ኢዴፓ ትኩረት የሚሰጣቸው ጉዳዮች

ሀ- ኢትዮጵያ ለአጠቃላይ የኢኮኖሚና የፀጥታ ህልውናዋ ዋስትና የሚሆን የባህር በር እንዲኖራት የሚያስችል ህጋዊና ዲፕሎማሲያዊ ጥረት ያደርጋል፡፡

ለ- በውጭ አገር የሚኖሩና በተለያየ ምክንያት ዜግነታቸውን የቀየሩ ትውልደ ኢትዮጵያውያን የተሟላ የኢኮኖሚና የፖለቲካ መብት ባለቤት ለመሆን የሚያስችላቸው የጥምር ዜግነትን የሚፈቅድ ሕግ እንዲኖር ይደረጋል፡፡

ሐ- የኤርትራንና የኢትዮጵያን ሕዝብ ግንኙነት የሚያጠናክሩ፣ በሂደትም ሁለቱ ሕዝቦች ወደ ታሪካዊ አንድነታቸው እንዲመለሱ የሚያስችል ሕጋዊና ሰላማዊ ጥረት ይደረጋል፡፡

መ- ጎረቤታችን የሆነችው ሶማሊያ የተረጋጋ መንግስትና ስርአት እንዲኖራት ኢትዮጵያ አስፈላጊውን ድጋፍ ታደርጋለች፡፡ በሶማሊያ በኤርትራና በደቡብ ሱዳን አካባቢ የኢትዮጵያን ጥቅም የሚነኩ እንቅስቃሴዎች እንዳይጠናከሩ አስፈላጊው ጥንቃቄና ጥረት ሁሉ ይደረጋል፡፡

ሠ- ኢትዮጵያ ከጐረቤቶችዋ ጋር ያላት የድንበር ውዝግብ የጋራ ጥቅምን መሠረት ያደረገ ዘላቂ መፍትሄ እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡ የድንበር ተሻጋሪ ወንዞች ጉዳይ የጋራ ጥቅምን መሠረት ያደረገ ዓለም አቀፍ ስምምነት እንዲደረግበት ይደረጋል፡፡ ኢትዮጵያ ከጐረቤቶቿ ጋር ጥብቅ የኢኮኖሚ ትስስር እንዲኖራት ይደረጋል፡፡

**2007 ዓ.ም**

## ዛሬም ይቻላል!

## ኢዴፓ-የዛሬውና የወደፊቱ ትውልድ ፓርቲ!

# 2007 ዓ.ም